የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፸፪
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Eighth Year No.72
Addis Ababa September 11, 2015


ማውጫ


በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ደንብ......................ገፅ ፩


CONTENT


THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT TRAFFIC MANAGEMENT AGENCY REGULATION...............................PAGE 1


## ደንብ ቁጥር ፸፪/፪ሺ፯

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ

የከተማውን ትራፊክ ፍሰት ለማሳለጥና ተደራሽ ለማድረግ፣ የመንገድ ትራፊክ ደህንነቱን ችግር መፍታት በማስፈለጉ፤

በመረጃ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የትራፊክ አመራር ስርዓት ለመዘርጋት፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን በመለየት ለማልማት፣ ለማስፋፋትና ለማስተዳደር በማስፈለጉ፤

እንዲሁም የከተማውን የትራፊክ መረጃ መሰረት ያደረገ የህብረተሰብ ግንዛቤ በመፍጠር የትራፊክ ደህንነትን ለማረጋገጥ የትራፊክ ሕግን በአግባቡ ማስከበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር ፵፫/፪ሺ፮ አንቀጽ ፵፯ ድንጋጌ መሰረት የተቋቋመና ስልጣንና ተግባራት የተደነገገ በመሆኑ፤

## Regulation No.72/2015

## A Regulation to Provide for the Organization and Procedure of the Addis Ababa City Government Traffic Management Agency

**Whereas,** it is found necessary to facilitate the traffic flow creating accessibility so as to reduce the traffic safety problems;

**Whereas,** it is found necessary to install traffic information system supported by technology, there by identifying, developing, expanding and administering the terminals;

**Whereas,** it is found necessary to respect the traffic laws properly by creating awareness among the community to insure traffic safety;

**Whereas,** the Traffic Management Agency has been established according to Proclamation No. 43/2014 Article 47 and its power and function determined thereof;

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀፅ ፳፫(፩) (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ አንቀጽ ፹፬ ድንጋጌ መሰረት የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፸፪/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. «ከተማ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
፪. «አስተዳደር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
፫. «ቢሮ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤
፬. «ኤጀንሲ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ነው፤
፭. «መንገድ» ማለት ለማናቸውም ተላላፊ ክፍት ካልሆነ የግል መንገድ በስተቀር ተሽከርካሪዎች በተለምዶ የሚጠቀሙበት ማናቸውም ጎዳና፣ የከተማ መንገድ፣ አውራ ጎዳና ወይም መተላለፊያ ነው፤
፮. «ትራፊክ» ማለት በማናቸውም መንገድ ላይ አንድ ወይም ብዙ ሆነው የሚተላለፉ እግረኞች፣ እንስሶችና ተሽከርካሪዎች ናቸው፤

**Now, therefore,** in accordance with Article 23(1) (f) of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003 and Article 84 of the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Services Organs re-establishment Proclamation No. 35/2012 Cabinet of the City Government issued this Regulation as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "A Regulation to Determine the Organization and Procedure of the Addis Ababa City Government Transport Management Agency No.72/2015."

### 2. Definitions

In these regulation unless the context requires otherwise:

1. **"City "** means the Addis Ababa City;
2. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Bureau"** means the Addis Ababa City Government Road and Transport Bureau;
4. **"Agency"** means the Addis Ababa City Government Traffic Management Agency;
5. **"Road"** means any road , street, highway or any other travel route customarily used by vehicle other than private roads not open to all traffic;
6. **"Traffic"** means one or more pedestrians, animals and vehicles that travel on a road;

፯. ‹‹ተሽከርካሪ›› ማለት በመንገድ ላይ የሚሄድ ጋሪ፣ ሰረገላ፣ ብስክሌት፣ ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ግማሽ ተሳቢና፣ ተሳቢ ናቸው፤

፰. ‹‹የትራፊክ ስርዓት›› ማለት በአንድ በተወሰነ ቦታ የሚደረግ የትራፊክ እንቅስቃሴና እንቅስ ቃሴው የሚመራበት የሰው ሃይል፣ የመሣሪያዎ ችና የአሠራር አግባብ ቅንጅት ነው፤

፱. ‹‹አዋጅ›› ማለት የአዋጅ ቁጥር ፵፫/፪ሺ.፮ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ.፬ ነው ፤

፲. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. <u>የፆታ አገላለፅ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ አገባቡ ልዩ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ለሴትም ጾታ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፬. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በከተማው አስተዳደር የትራፊክ እንቅስቃሴዎችና የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፭. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

፩. የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በከተማ በማዕከል ይሆናል፤

፪. እንደ አስፈላጊነቱም በከተማው የተለያዩ ቦታዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፮. <u>ዓላማዎች</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የከተማውን ትራፊክ ፍሰት የተሳለጠና ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ፤

፪. ማናቸውንም የመንገድ ትራፊክ መረጃዎችን ማደራጀትና ተደራሽ ማድረግ ፤

7. **"Vehicle"** means any kind of wheeled vehicle, for use of roads that classified as carriagee, bicycle, motor vehicle semi trailer and a trailer;
8. **"Traffic system"** means a system in a specified place where traffic movement is managed using human and material resource in a co-ordinate way;
9. **"Proclamation"** means Proclamation No. 43/2014 that amended Proclamation No. 35/2012;
10. **"Person"** means natural or juridical person.

**3. <u>Gender Reference</u>**

In this regulation, unless the context demands otherwise, any expression in the masculine gender shall also apply to feminine gender.

**4. <u>Scope of Application</u>**

This regulation shall be applicable to Addis Ababa City Traffic Movement and Vehicle Terminals.

**5. <u>Head Office</u>**

1. The head quarter of the Agency shall be at the city center;
2. It may have branch office in different areas of the City, where necessary.

**6. <u>Objectives</u>**

The agency shall have the following objectives:

1. To make the City's traffic flow efficient and safe;
2. Organizing every road traffic information and making same accessible to the society;

፫. ድንገተኛ የከተማ ትራፊክ ክስተት ሲያጋጥም አፋጣኝ መፍትሄ መስጠት፡፡

## ክፍል ሁለት

## አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር

**፯. የኤጀንሲው አደረጃጀት**

፩. ዋና ዳይሬክተር፣

፪. ሁለት ምክትል ዳይሬክተሮች፣ እና

፫. አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

**፰. የኤጀንሲዉ ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው በአዋጁ የተሰጡ ግዴታዎችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩. በትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ በሕግ መሠረት የሚጣል ቅጣት ራሱ ወይም ውክልና በሚሰጠው ተቋም አማካኝነት በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ሕግ መሠረት ይሰበስባል፣

፪. የከተማውን ትራፊክ አመራርና አስተዳደር ሥራ ይፈጽማል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፣ ለአገልግሎቱ ሥልጠት የሚያግዙ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ይተገብራል፣

፫. ስለከተማ አስተዳደሩ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሁም የትራፊክ ሥርዓት ለሚመለከታቸው አካላት መድረኮችን በማመቻቸት ግንዛቤ ይፈጥራል፣

፬. የትራፊክ ኢንጂነሪንግ ሥራዎች ይሠራል፣ ችግር ያለባቸውን መንገዶች በመለየት የዲዛይን፣ የምልክት አመላካች ሥራዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፣

፭. የፖርኪንግ አገልግሎት ፈቃድ ያድሳል፣ ፖርኪንግ መናኸሪያዎችን አገልግሎት ያስፋፋል፣ የተሽከርካሪ ፍሰት ይቆጣጠራል፣

3. Give immediate solution where traffic incidence occurs.

## PART TWO

## ORGANIZATION, POWER AND FUNCTION

**7. Organization of the Agency**

1. General Director;
2. Two deputy directors; and
3. Necessary workers and working departments.

**8. Power and Function of the Agency**

In order to discharge the duties provided in the proclamation, the Agency shall have the following powers and functions:

1. Collect, by itself or through legally delegated institution, fine imposed on violators of traffic regulation in accordance with law based on finance law of the City Government;
2. Perform and superiorly control the traffic management and administration of the City; design and implement techniques that help towards effectiveness of the service;
3. Create awareness to the concerned bodies on the transport service as well as the traffic system of the City Government by arranging forums;
4. Perform traffic engineering works; identify roads that have problem and cause fulfillment of design and road signs;
5. Renew parking service license, expand parking station service, build parking facilities, control vehicle flow, install in

## ፲. የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር

ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ለኤጀንሲው የተሰጡትን ስልጣን፣ ተግባራትና ሀላፊነቶች ያከናውናል፤

፪. የኤጀንሲውን ስራዎች ያቅዳል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

፫. ሠራተኞችንና ዝቅተኛ የስራ ሃላፊዎችን በህጉ መሰረት ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፤

፬. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ለሚደረገው ግንኙነት ኤጀንሲውን ይወክላል፤

፭. የኤጀንሲውን የሥራ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም በጀት በማዘጋጀት በቢሮው አስገምግሞ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

፮. ኤጀንሲውን ውጤታማ ሊያደርጉ በሚያስችል ስትራተጂያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፯. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የስራ ድርሻውን ለምክትል ዳይሬክተሮቹ በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፣

፰. በቢሮው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፲፩. የምክትል ዳይሬክተሮች ስልጣንና ተግባራት

ተጠሪነታቸዉ ለዋና ዳይሬክተሩ ሆኖ ምክትል ዳይሬክተሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

፩. የኤጀንሲዉን ዕቅድ በማዘጋጀትና ተግባርና ሀላፊነትን ለመወጣት ዋና ዳይሬክተሩን በማገዝ ይሠራሉ፤

## 10. Powers and Functions of the General Director

The General Director shall have the following powers and functions:

1. Perform the power and functions of the Agency  enshrined in the Proclamation and this Regulation;
2. Plan, manage and control activities of the Agency;
3. Employ and dismiss workers and low level leaders according to the law;
4. Represent the Agency in relationships with a third party;
5. Prepare the agency work and financial plan implement if approved by the concerned body;
6. Give attention to strategic issue to the agency be more effective in implement the working procedure and follow up the implementation;
7. Where necessary delegate his work for the deputy directors;
8. Perform other tasks assigned to him by the Bureau.

## 11. Power and Function of Deputy Directors

Being accountable to the General Director, the deputy directors shall have the following powers and functions:

1. Work assisting the General Director in preparing plan and discharging the duties and functions of the Agency;

ከትራንስፖርት ባለስልጣን ጋር በመተባበር የጭነት መንቀሳቀሻ ፈቃድ ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፮. የመንገድ ትራፊክ ክስተት መረጃ ያደራጃል ያሰራጫል፣ ለሚመለከታቸው አካላት የሥልጠና ተግባራትን ያከናውናል፤

፯. የትራፊክ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ይሰራል፤

፰. የከተማው ትራፊክ ስርዓት ማሻሻል የሚረዱት የቴክኖሎጂ አውታሮችን ይዘረጋል፣ ያስተዳድራል፣ ተደራሽነታቸውንም ያረጋግጣል፤

፱. ከትራፊክ አመራር እና ደህንነት ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፱.የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ይፈፅማል፡-

፩. የትራፊክ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ይሰራል፤

፪. የከተማውን የመንገድ ትራፊክ ይቆጣጠራል፣ በትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ በሕግ መሠረት የሚጣል ቅጣት ራሱ ወይም ውክልና በሚሰጠው ተቋም አማካኝነት በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ሕግ መሠረት ይሰበስባል፤

፫. ሌሎች ከኤጀንሲው ተለይተው የሚሰጡት ተግባራትን ያከናውናል፡፡

coordination with Transport Authority system of goods movement license control;

6. Organize and disseminate road traffic incident data; perform training functions to concerned bodies;

7. Perform awareness creation works by preparing traffic educational programs;

8. Install technological infrastructure that help improve the traffic system of the City; administer same and ensure accessibility thereof;

9. Perform such other activities related to traffic management and security.

## 9. Power and Function of Branch Office

The branch office, being accountable to the Manager of the Agency, shall have the following powers and functions:

1. Perform awareness creation works by preparing traffic educational programs;

2. Supervise road traffic of the City; collect, by itself or through legally delegated institution, fine imposed on violators of traffic regulation in accordance with law based on finance law of the City Government;

3. Perform such other activities specifically designated by the Agency.

፪. የኤጀንሲዉ ዋና ዳይሬክተር በሌለበት በእርሱ ተለይቶ የተወከለዉ ተክቶ ይሠራል፤

፫. የተመደቡበትን የሥራ ክፍልና · ዘርፍ ዕቅድ በማዘጋጀት ለኤጀንሲዉ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

፬. ሌሎች ከዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናዉናሉ፡፡

## ፲፪. <u>የዋና ዳይሬክተሩና ምክትል ዳይሬክተሮች አሿሿም</u>

የኤጀንሲዉ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዳይሬክተሮች በከተማዉ ከንቲባ ይሾማሉ፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## ፲፫. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፬. <u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በከተማው አስተዳደር ይመደባል ፡፡

## ፲፭. <u>የሂሳብ መዛግብት አያያዝ</u>

፩. ኤጀንሲው በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሰረት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው አስተዳደር ዋናው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

2. The deputy director expressly delegated shall substitute the General Director in case of his absence;
3. Prepare and submit to the Agency the plan of the department and sector assigned and implement same upon approval;
4. Perform such other functions assigned by the General Director.

## 12. <u>Appointment of General Director and Deputy Directors</u>

The General Director as well as the Deputy Directors shall be appointed by the Mayor of the City.

## <u>PART THREE</u>
## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

## 13. <u>Duty to Cooperate</u>

Every person shall have the duty to cooperate for the implementation of this regulation.

## 14. <u>Budget of the Agency</u>

Budget of the Agency shall be allocated by the City Government.

## 15. <u>Keeping of Books of Account</u>

1. The Agency shall keep complete and accurate books of account in accordance with the finance administration law of the City Government;
2. Books of accounts of the Agency shall be inspected by the Auditor General of the City Government.

**፲፮. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>**

ይህንን ደንብ ስራ ላይ ለማዋል ቢሮው መመሪያ የማውጣት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

**፲፯. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሽከርካሪዎች ማቆሚያና ጥበቃ አገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበር ማደራጃ ደንብ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፩ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፰. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከመስከረም ፫ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**ጳጉሜ ፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**16. <u>Power to Issue Directive</u>**

The Bureau shall have power to issue directives for the implementation of this Regulation.

**17. <u>Inapplicable Laws</u>**

1. The Eestablishment of the Car Parcking and Guarding Service Cooperative Regulation No. 15/2009 is here by repealed.
2. Any regulation, directive or customary practice which is inconsistence to matters covered in this regulation shall have no effect.

**18. <u>Effective date</u>**

This regulation shall enter in to force as of 14th day of September 2015.

**Done at Addis Ababa**
**On this 11th day of September 2015**

**Diriba Kuma**
**Mayor of Addis Ababa City**